# ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያኖች በአሁኑ ጊዜ ያላቸው ልባዊ ግንኙነቶች እና የአገራችን እድል?

የለንደኑ የሰብአዊ መብት አስከባሪ ድርጅት አምንስቲኢንተርናሽናል እንዲሁም ሌሎች እንደሚሉት ኢትዮጵያ በጦር ወንጀለኝነት ከሶማሊያ የሽግግር መንግሥት ጋር አብረው የሚከሰሱ ይሆናሉ ሲል አስተያአየቱን ሰቷል፡፡

ለመሆኑ በዲሴምበር ወር 2006 ኢትዮጵያ ወደሞቃዲሾ ሳትሄድ በፊት ገና በመንገድ ላይ እያለች የዓለም ሕዝብ ሳይቀር ፍርሃት ተጫጭኖት እንደነበረ ያመለክተን ነበር፡፡ ያም እስከ አፍ ጢማቸው የታጠቁት ኢስላሚስቶች በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ አገሮችን በሙሉ ወደጦርነት ውስጥ የሚያስገባቸው ነገር ይሆናል በሚል፡፡

ኢትዮጵያም ላይ የመጀመሪያ ኢላማቸውን በማድረጋቸው ያሁሉ ልፍለፋና ጠዋት ማታ የውጭ አክራሪዎች ሶማሊያ ጥሪ እያደረገችላችሁ ነው፡፡ ባስቸኳይ ድረሱልን ኢትዮጵያ የምትባል አገር ቅኝ ገዥዎች የፈጠሯት አገር ኦጋዴንን ገንጥላ ወስዳብናለች፡፡ ቀጥሎም ኢትዮጵያ የምትባል አገር በዚህ አካባቢ አልነበረችም፡፡ በማለት አዲስ አበባንም ሄደን እንይዛታለን ሲሉ አሁንም የዓለም ማስሜዲያዎች ለኢትዮጵያም ሆነ ባካባቢው ላሉት አገሮች ምንያህል ስጋትን የሚያመነጭ እርምጃ እንደሚካሄድ በዚያ ስፋራ ይገልጹ ነበር፡፡

በመጀመሪያ ያች አገር ለ16 ዓመት መንግሥት አርዓት ስትከተል ሁለመናዋም በአናርኪዎች መንፈስ ተበክሎ በአለም ላይ ለሚሰራችህው እጽ ማስተላለፊያ ሆና በማገልገል ብሎም የባህር በሮቾአም የማንም አናርኪ መመላለሻና ከልካይ የሌለበት ዓለም አቀፍ አሸባሪዎች መለማመጃ ሆና ኖራለች፡፡

አሁን ያየታሰበ ነገር ሊቀጥል ቢችል ኖሮ በዚያ በምሥራቅ አፍሪቃ አካባቢ ምን ሁኔታ ይፈጠር ነበር? እንግዲህ ማሰብ ያለው በዚያ ላይ ነው፡፡ አሁን ተመልሰው ይህን የመሰለ ወንጀልን የመሰለ የመከላከል ነገር ተፈጽሟል ብለው ሲናዘዙ ሲሰሟቸው ለመሆኑ ምን ለማለት ፈልገው ነው? ወይስ ምን ለመሆን? አለም አቀፍ ሕግ ራሱን የቻለ የተባእብሩት መንግሥታት ቻርተሮችን ተከትሎ የሚፈጽም እንጂ እንዲሁ በወሬ ተነስቶ በአንድ አገርም ሆነ መንግሥቶች ላይ ያለምክንያት ክስ የሚመሰረት ያለመሆኑን እንኳን አጣርተው ሊያውቁት አልቻሉም፡፡

ዛሬ በሞቃዲሾ አነሰም አደገም የሶማሊያ ሕዝብ መንግሥት ኖሮት ባንድራውን ሰቅሎ በመንግሥትነትም ታውቆ ዲፕሎማቶቹንም ቢበዛ በአፍሪቃ በኬኒያ በዩጋንዳና በኢትዮጵያ አሰማርቷል፡፡ ያንን የመሰለ ክፍተኛ ክፍያ የተከፈለበትን እርዳታ ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ህዝብ አድርጋለች ለራሷም ሰላሟን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች፡፡ መመስገን ሲገባት ይህን የመንደር የስኒ ገልባጮች ወሬን እነማን እንደሚያናፍሱትም ይስተዋላል፡፡

ቁምነገሩ ግን እንደዚያ ሳይሆን በተለይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችም ሆኑ ጽንፈኞች ጭምር ኢትዮጵያ መኖር አለባት የሥልጣን ናፍቆታችሁን ለጊዜውም ቢሆን ቻል ልታደርጉት ይገባል፡፡ ካለበለዚያ ግን በመጀመሪያ ችግሮች በኢትዮጵያ ቢደርሱ ወይም ቢቻላቸው በቅድሚያ የሚጎዳው ሕዝቡ ነው፡፡ ያንን ጠንቅቆ መገንዘብ ይገባል፡፡ ሌላው ደግሞ ሻጥር ዛሬም ሻጥር ክፉ አስተሳሰብ ማን አለብኝ አነጋገሮችና ዘረኝነቶችን የሚያንጸባርቁ አባባሎችን መተው ቢቻል አገራችን ይህ ተራ በተራ እየመጣ የሚያስቸግራትን የውጭም ይሁን የውጭ ጠላቶቿን ማሸነፍ ይቻላታል መደማመጥ እስካለ ድረስ ነው ያም ሊሆን የሚችለው፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ሁሉም በየመንገዱ ተጣጥሎ የሚገሰግስ መደማመጥ አልባና ስምምነቶችንም ወደ አልታሰበ አቅጣጫዎች ለመቀየር በተለይ የዲያስፖራው ተቃዋሚ ነኝ የሚል ስብስብ የሚያናፍሱት የቅዠት ወሬያቸው ለአገሪቱ መኖር ሲባልና ብሎም ለዕገቷና ከድሕነት ለመውጣት ለምታደርገው ርብርቦሽም ላይ አብሮ ባንድ ላይ መካፈል ይገባል፡፡ እውነትም የውጭው ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ካላችሁ? አለበለዚያ ግን የሻዕቢያ ስማበለው የሆነ የገደል ማሚቶ የሚመስል የጩኸት ድምጽ ማሰማታችሁ ለኢትዮጵያ አድም ጥሩ መንገዶችን እንደማይከፍትላት ማወቅ ከቻላችሁ አዋቂ ናችሁ በሚል የአገራችሁ ህዝብ ይገምትላችሁ ነበር፡፡

በሶማሊያም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ይህን ሁሉ ኃተታዎችን በማንጠልጠል የወሬ እስሽቅድድሞችን እያደረጉ የሚገኙት እነማን እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የኤርትራው ሻዕቢያ እጅግ ብዙ ምላሶችና ጥርሶች አፎች ያሉት ድርጅት ነው ያም አፈጣጠሩ እንደዚያ ስለሆነና በመሆኑም፡፡ ያማ ባይሆን ኖሮ ኢትዮጵያ በሻዕቢያ አገር ሄዳ አንድም ነገር አላደረገችም ልታደርግም አትፈልግም፡፡ ሻዕቢያ ያለው ፍራቻ ምን ላይ እንደሆነ አይታወቅም አልታወቅምም ብሎ ሲያስቸግር ይሄው ብዙ ዓመታት አስቆጠረ፡፡

በመጀመሪያ አብሮ የሚኖሩ የቀረበ ግንኙነትና ወንድማማችነት ያላቸው ሕዝቦች ከመረብ ወዲያም ሆነ ወዲህ ይኖራሉ፡፡ ጉዳዩን ልክ የቤተሰብ ጉዳይ አድርጎ ሁሉም ነገር በአገር ሽማግሌዎች ፍጻሜ አልባ እንዲያገኝ ከመጣር ይልቅ ዘሎ ጽንፈኞች ሰብስቦ በኢትዮጵያ ላይ አምባጓሮ ለማስነሳት ጉድጓድ ከመማስ ይልቅ ተቀራርቦ ተድሰማምጦ ቢሰራ ነበር ይሄ ሁሉ ከፊታችን የሚገኘው ችግር አይደርም ነበር፡፡ ያለው ሁኔታ ግን እጅግ የሚያበረታታ ሳይሆን ደካማዎች የሚያስቡትን የሚያስብ ተንኮለኞችንም ያሰባሰበ ሻዕቢያ ያን የቀድሞውን ጸባዩን አሁን መንግሥት እንኳን ሆኖ ሳለ ያልተወውና በተለይ ብሶበት ህመሙ ሌት ተቀን እያስገዘፈው ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ አያስፈልገውም፡፡

በቀላሉ ኢትዮጵያ በሶማሊያ ሠላም እንዲወርድ በሚል በሞቅዲሾው ስብስብ ላይ ሁሉም የሶማሊያ አንጃዎችን ተቀብሎ የሽግግር መንግሥታቸው ጉባዔውን እንዲያደርግ ከፍተኛ አስተዋጾ አድርጋለች፡፡ ሳምንት ሳይሞላው ደግሞ አስመራ ሌላ አይነት መንገድና ብሎም እቅድ ያላቸው እነ ሸህ ጣሂር ሸህ አሕመድንና ሁሴን አይዲድን የመሳሰሉ ጎራዎችን አሰባስባ የኢትዮጵያን እቅድ አፈር መሬት ለማስገባት እየሰራች ትገኛለች፡፡ በዚያም ላይ የኦጋዴን ጽንፈኞችን፡፡ የኦነግ ጋንጊስተሮችን፡፡ የአርበኛ ግንባሮችን፡፡ እነዚህም AFD ተብለው ስም ተሰይሞላቸው ኢትዮጵያን እየገቡ እንዲያመሳቅሉ እያደረገ ነው ሻዕቢያው?

ታዲያ በምን ዓይነት ሁኔታ በዚያች አካባቢ ሰላም ይመጣል? በሁለቱም ሕዝቦች መሃከል አሌ የማይባል መቀራረቦች ሊኖር የግድ የሚልበት ወቅቱ አሁን ነው፡፡ ያለህዝቡ ፈቃድ የሚደረጉ ማናቸውምንም ስሕተቶች ህዝቡ እንዲታረሙ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ይህ ነገር እየከረረ የሚሄድ ከሆነ ለሁለቱም አገሮች አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሊጥላቸው ስለሚችልና የተጀመረውም የዔኮኖሚ እድገትና ከድህነት ለማምለጥ የሚደረገው እርምጃዎች ሁሉ ይቀራሉ ማለት ነው፡፡ አሁንም ተመልሶ የሚጎዳው ሕዝቡ ይሆናል ማለት ነው፡፡

በነዚህ ነጥቦች ላይ ህዝቡ ሊያስብና የሚደረግበትን ማናቸውንም ዓይነት ተጽዕኖዎችን ማክሸፍ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ ከዚያ የተቀራረቡ አገሮች ሆነው አብሮ በመስራት በዚያች በአሉበት የአፍሪካ ክፍል ማንም ሊመጣጠነው የማይቻለው የኤኖሚ እድገቶችንና ብሎም መቀራረቦችን ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ይህን የቀረ የጦርነት አባዜዎችንም ህዝቡ ከቤቱ ወጥቶ ሊያወግዘው ይገባል? በእደዚያ ዓይነት ሁኔታም ጭምር ሊታሰብበት ይገባል ነው፡፡ ያሳይሆን ይቀርና በሌ አቅጣጫ የጥፋት መንገዶች አሁንም የሚቀጣጠሉ ከሆነ እንዲሆኑም እቅዶች የሚወጡላቸው ከሆኑ ለማንም የማይጠቅም ሁኔታ በዚያች በምሥራቅ አፍሪቃ ምድር ብዙ ውድመቶችና ብሎም መበታተኖች ከዚያም ልክ እንደሶማሊያ የአልታሰቡ የአናርኪስቶች መናኸርያዎች እንደሚሆኑ ላፍታም ቢሆን መጠራጠር አንችልም፡፡

ስለሰላም አንዳቸውም በዚያ አካባቢ የሚያወሩ አይስተዋሉም፡፡ ኢትዮጵያ ብቻዋን ስለሰላም ልትናገር አይሆንላትም፡፡ ሻዕቢያ ይሄን ሁሉ ጉድ እንደሚያደርግ ከዳርፉር እስከ ሞቃዲሾ ደረስ የሚያደርጓቸውን ክንውኖች ብዙዎች ያውቃሉ እንኳን በሚል ሳያፍሩ ሳያስቡበትም እንዲያውም ይባስ ብለው እነ ሸህ አህመድና አይዲድን በአስመራ ከተማ እንዲኖሩና አገራቸውን የበለጠም እንዲያጠፏት እነሻዕቢያ የቱን ያህል እየረዱቸው መሆኑንም ለማገናዘብ የሚያስችል መንፈስ በሻዕቢያዎች ላይ እግዚአብሔር ፈጥሮላቸው ይሆን? ነገሩ ሲመለከቱት የሚያስገርም ነው፡፡ እንዴት ሰላም ሊመጣ ይቻለዋል በዚህ ዓይነትና በግትርነት የሚካሄዱት አስተዳደርና መንግሥት እንዴትስ ብሎ ይቆማል ብለው በትንሹ ቢሆን እንኳን ሊገነዘቡት ሞክረውት ይሆን፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ቻይነት እንጂ ሻዕቢያ በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ የሆነ ስህተቶችን ቀን ከሌት ሰርቶ እየፈጸመም ነው ያንንም አፈጻጸሙን ዘወትር እንደቀጠለበት ነው? እልህም ይመስላል፡፡ በመጀመሪያ ሻዕቢያ ከኢትዮጵያ ሲገነጠል ኢትዮጵያ የምትባለው አገርን ተገንጥዬም እየኖርኩ በኤኮኖሚዬ ግን ያች አገር የሻዕቢያ ገባሪና ባጀቶችንም አፍላቂና ገንቢ ትሆንልኛለች ብሎ የሚያስብና ያሰበም ያስመስልበታል፡፡ እንግዲህ አንድ አገር ነጻሕነት መርጫለሁ ብሎ ካሰበና ካለ ኢትዮጵያ ያችን አገር ማወቅ ያለባት ልክ እንደ ኬኒያ ዩጋንዳና ሱዳን ታንዛኒያና ሶማሊያ ጂቡቲ አይነት እንጂ ከዚያ አልፋ የሻዕቢያን ጓዳ ለማበጀት ለማጠናከር አስባና ገብራ ለመኖር እንደማትፈልግ ሻዕቢያ አላወቀውም ማለት ያሰኛል?

በአጋጣሚ ሆኖ በመጀመሪያ ዳርድንብርን ሳያካልሉ ሳያውቁትም አገሬ ከዚህ እስከዚህ ነው ብሎ ማልሰቡም ስህተት የተሰራው ዛሬ ሳይሆን ከሻዕቢያ አፈጣጠር ቀን ጀምሮም መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ምክንያቱም ሻዕቢያና የጠገበ ፈረስ አንድ አይነት አስተሳሰብና አመለካከት አላቸው እሱ ከጠገበ ሁሉም የጠገቡ ይመስላቸውና

ግልቢያቸውን ይጀምራሉ ያም ግልቢያ ጦርነትን መስራት ይሆናል ያም ጦርነት የሰውን ሕይወት የሚቀጥፍ አይመስለውም፡፡ ያማ ባይሆን ኖሮ በሓይደር የሕጻናቶች ትምህርት ቤት ላይ ክላስተር ቦንብ አዝንቦ እነኛን ሁሉ ሕጻናት እንደት ይገላቸው ነበር? እንግዲህ የማያስብ ጭንቅላት እዚያ አስመራ ከሻዕቢያ ቁንጮ ላይ ወጥቶ አልወርድ ብሎ እያስቸገረ ይገኛል፡፡ ታዲያ ኤርትራዊያኖች ያንን አስቸጋሪ ነገር ለምን አስወግደው ወይም ወደ ገነባው ቤቱ እንዲሳፈር አድርገው አሻግረው እነሱ በስምምነት ላይ ያበበች እና ብሎም ከጎረቤቶቿ ተስማምታ ራሷን ማሻሻል የምትችል አገር እንዴት ላይመሰርቱ እንዳልቻሉ ያስገርማሉ፡፡

በዚህና በሌላ አባባሎች ላይ ለወደፊቱ ሰፋ ያለ ሃተታዎችን ለማቅረብ እስከምዘጋጅበት ድረስ ለዛሬ የቀረበው በተለያዩ አቅጣጫዎች የሚያመላክቱ ያገራችንና የኤርትራንም ችግር ጨምሮ አውግተናል፡፡ ነገር ነገርን ነገር ነው የሚያነሳው ይባላል፡፡ ለመሆኑ አንድ አገር የሌላውንም መብት ሳትነካ የራሷም ሳይነካባት ለመራመድ አይቻላትም ወይ? ታዲያ የኤርትራ መሪዎች ለምን ይሆን በኢትዮጵያ ላይ ይሄን ሁሉ ወንጀላዊ ሥራዎቻቸውን ለመስራት መንፈሳቸውን በማስጨነቅ ሳይሰለቻቸው አንድን አገር ለማጥፋት ከፍተኛ ሰው ሰራሽ ወንጀሎችን በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ እየፈጸሙ ያሉትና ለስራቸውም ትንሽ ቅሬታ የሌላቸው ሉዓሙን ያወለቁለት ፈረስ የሚጋልበውን ያህል አገራቸውን አስመስለው ስለሌላ አገር ለመናገር የሚፈልግት? ምን ጠቀሳቸው እነሱን ኢትዮጵያን አንፈልጋትም አንወዳትም ብሎ ህዝቡንም በመሳሪያ አፈሙዝ አፉን ሸብቦ በ1993 እ ኤ. አ ነጻሕነት ካልሆነም ባርነትን የትኛውን ትመርጣላችሁ ብሎ ገንጥሎ ወስዷል? ነገር ግን እንኳንስ አገርን በአገራችን በአጥር እንኳን ሰዎች ሲገናኙ ቁጭ ብለው መክረው አጥር ያንተ እስከዚህ ድረስ የኔ ደሞ እስከዚያ ድረስ ተባብለው ያሰሩት ውል እስከ ልጅ ልጆቻቸው ድረስ ረዝሞ ይሰራበታል፡፡ አገር ሲመሰረት ደግሞ ልዩ ገጽታዎች አሉት እነኛን ሁሉ በወቅቱ አስበው ሳይሰራ በመቅረቱ ዛሬ የጦእነቱ መነሻ የሆነው ያጉዳይ ነው ይባላል፡፡ ታዲያ ስሕተቱ የማን ነበር?

ብቻ ወደፊትም ይሁን ለአሁኑ ላለንበት ጊዜ ሠላም እንዲሁም ፍቅር በዚያ አካባቢ እንዲፈጠር እመኛለሁ፡፡ ሰላም ለአገራችንም ሆነ ከመረብ ወዲያ ማዶ ለምትገኘው ጎረቤት አስፈላጊዎች ናቸው ያንን ሰላም ግን እርስበርስ እየተወነጃጀሉ ሳይሆን ሊመጣ ሊገኝ የሚችለው ተቀራርቦ አብረው በመመካከር ሲሰሩና የርስበርም መተሳሰቦች ሲኖሩና እነኛንም ለማግኘት ቆርጦ ለመስራት ራሳቸውን ሲያዘጋጁ ብቻ ነው፡፡ አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ያለመግባት ራሱን የቻለ ጥሩ የትብብርነት ጅምርነው ይባላል፡፡ እስቲ ያንን ለማድረግ እንኳን ቢሆን በ2ቱም በኩል ቅርርብ ይጀመር ለዚያ አካባቢ አንዱ ሌላውን ገድሎ የሚያገኘው ውጤት የለም፡፡ ሁለቱም የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው በሁለቱም መሐከል ያጀግና ይሄ ፈሪ ሊባል ሊያስብለውም አይቻልምና፡፡

መከተ ሰው 14/09/07